# አዬ ቃሊቲ ! ስንቱን ጉድ ይዘሽ ነበር

ከኃይለ ልዑል ግርማ

ይድረስ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በአገርም በውጭም ላላችሁ::

እንኳን ለ2000 ዓመት ወይም ለኢትዮጵያውያን እስራ ምዕት አደረሳችሁ እያልኩ ለሀገራችንና ለሕዝባችን መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ::

ካልደፈረሰ አይጠራም ይላሉ አበው ሲተርቱ:: አዎን ይደፍርስና ይጥራ:: እስከመቼ ጉምጉምታው፣ ሀሜታው፣ ውዥንብሩ ይቀጥላል:: የላላው ጠበቅ፣ የተወጠረው ተንፈስ፣ ያፈነገጠው ውልቅ፣ የጠነከረውም በርትቶ ይዝለቅና ትግሉ ይቀጥል:: የተነቃነቀ በሽተኛ ጥርስ ካልወቀ ነው የተባለው እየጠዘጠዘ፣ እራስ ምታት እያመጣ አላናግር፣ አላስበላ፣ አላስጠጣ እያለ ጤና ሲነሳ ውልቅ ይበልና ሰላም ማግኘቱ እንዴት ይመረጣል መሰላችሁ:: ወደ ጉዳዬ ልግባ::

የቅንጅት መሪዎችና አባላት በቃሊቲ ከታሰሩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተከሰተው የውስጥ ደባ ዛሬ አብሮ ተፈትቶ ስራውን ሊቀጥል ሲዳዳው "የለም ይበቃል" የሚባልበት ጊዜ ላይ ተደረሰና አቂም መለየት፣ እርምጃ መውሰድ ጊዜው ሳያልፍ የግድ ነው::

ትንሽ ወደ ኋላ ልውሰዳችሁ:: "መሪዎቻችን በታሰሩ በ5ኛው ቀን" ይላሉ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የቀድሞው ወያኔ እና የዛሬው የቅንጅት ወያኔ "ባገር ቤት ያለው አመራር ስለታሰረ አመራሩን ውጭ ያለው የቅንጅት ደጋፊ ይረከብ" ሲባል መጀመሪያ የተቃወምኩ እኔ ነበርኩ ይላሉ መጀመሪያ ላይ ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ሲባል ያልጠበቁት ተቃውሞ ሲመጣባቸው ጊዜ:: በሳምንቱ ደግሞ እንዴ መሪዎቻችን ታቦት ናቸው እንዴ በሌላ የማይተኩት? እኛም እኮ መምራት እንችላለን አሉ ለንደን ኢንግላንድ ላሉ የቅንጅት ደጋፊ አባላት:: ከጥቂት ወራቶች በኋላ ደግሞ ዋሽንግተን ዲሲ ብቅ አሉና የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ስብሰባ ላይ ሳይጋበዙ ተገኙ:: ማን ጠራቸው ማናቸው የሚል ጥያቄ ሲቀርብ አቶ ብርሃነ መዋ የእኔ እንግዳ ናቸው ብለው ትንሽ ንግግር ቢያደርጉ ቢፈቀድልኝ ብለው መንገዱን አመቻቹ:: የጠረጠረ የለምና በአቶ ብርሃነ መዋ በኩል ስለመጡ በይሉኝታ ዝም አሉ አብዛኞቹ:: ይህ የሆነው በጄንዋሪ 2006 ሲሆን የተልኮል ጥንስሱ ቀስ በቀስ አድጎ በሜይ አጋማሽ 2006 ላይ ራስ የሚያሳመም በሽታ ሆነና ቅንጅት ኢንተርናሽናል አመራር የሚል ኮሚቴ ተብሎ መሾሙን አቶ ብርሃነ መዋ ከቃሊቲ መጣ የተባለ ባለቤት የሌለው የኢሜይል ሹመት አነበነቡት:: ሹመቱን የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ሳያውቁት ሳይነገራቸው ሊቀመንበሩ ትክክለኛነቱን ሳያረጋግጡ ተነገረ:: በአጣዳፊ በሻዕቢያው ኤልያስ ክፍሌ ድኀረ ገጽ በኢትዮጵያን ሪቪው ላይ ወጣ:: ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው በኤልያስ ክፍሌ ነው:: እንዴት ማን ላከለት ለምንስ? መልሱን በኋላ እናገኘዋለን:: ዛሬ ድብብቆሽ የለም ፍርጥርጥ አድርጎ የመሸበት ማደር:: ጀግኖች መሪዎቻችን እንኳን መታሰር መሞትም የማይፈሩ ናቸውና ለማንም አንፈራም:: ሕዝብ ያላወቀው በጎረቤት አገር ከተፈጸም እንጀምርና እነ አንዳርጋቸው ጽጌ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች በአስር ሺዎች በየካምፑ እስር ቤቱ ሲሰቃዩና ጥቂቶቹ አምልጠው ወደ ጎረቤት አገር ቢሸሹ አንዳርጋቸው ጽጌ ወደ ትግሉ ተቀላቀሉ እያሉ ከተሰደዱበት የጎረቤት አገር ወደ አስመራ እንዲሄዱ ያደርጉ ነበር:: ሀሰት አይደለም በህይወት ያሉ ይናገራሉ:: አስመራ ምን ሊያደርጉ እንደሚሄዱ አንዳርጋቸው ጽጌ ያስረዱን:: ካገር አገር ሲንከራተቱ የደረሱበት ያልታወቀ ወጣቶችን ቤቱ ይቁጠራቸው:: ትረፉ ያላቸው ተርፈው ታሪኩን ሊያወጉን በቁ:: ቅንጅትን ለመበተንና ለመከፋፈል ያላወሩት ያላነፈሱት የሀሰት ዜና እና ስም ማጥፋት የለም:: የእነርሱ ደጋፊ የሆነውን የቅንጅት ፓርቲ አባል ነህ እያሉ ከደጋፊው ጋር ሲያጋጩት ከርመዋል:: ካድሬዎቻቸውን 24 ሰዓት በፓልቶክና በተገኘው መድረክ ሁሉ ተመሳሳይ የሀሳት ዜና ያራግባሉ::

የገንዘብ ጉዳይ፤ ለምሳሌ ያህል እስከ ኦክቶበር 2006 ድረስ የሰሜን አሜሪካን ድጋፍ አመራርም ሆነ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር የነበሩት ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም ምክትል ሊቀመንበር ሆነው የወጣውን ወጪ ሁሉ በቼክ ላይ ሲፈርሙ ነበር:: አቶ

ብርሃነ መዋም ጸሀፊ ሆነው ወጪውን ያውቃሉ ዶክመንትም ይይዛሉ፤ ገንዘብ ያገርም ሌላ ሰው ነበር። ታዲያ ዛሬ 1 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር የት እንደደረሰ አይታወቅም ሲሉ ሻለቃን ብቻ ተጠያቂ ናቸው ከማለት በፊት እነዚህ ሰዎች በሙሉ በሃላፊነት የማይጠየቁበት ምን ምክንያት አለ? በኦክቶበር እነ ብርሃነ መዋ ሲታገዱ 250 ሺህ ዶላር በሌላ አካውንት መዛወሩን ሻለቃ ዮሴፍ ለሕዝብ ያስታወቁ ሲሆን ምክንያቱም የመስመር ልዩነት ተፈጥሮ ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም በቼክ ላይ ፈራሚ ስለነበሩ ገንዘብ የማውጣት ሥልጣን የነበራቸው በመሆኑ እንደነበር ገልጸዋል። ታዲያ አብረው ሲሰሩ ቆይተው ኃላፊነቱን በሻለቃ ዮሴፍ ላይ ብቻ መከመራቸው ሻለቃ ዮሴፍን በሀሰት ስም ለማጥፋትና ለማዋረድ፣ ከሊቀመንበርነታቸው ለማውረድ የታቀደ ደባ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታያል። አገር ቤትና በስደት ያለው እየተላከ ሲረዳ የነበረው ተረጂ እና ሥራ ሲሰራበት የነበረው አንዳርጋቸው ጽጌ ወይስ ብርሃነ መዋ ገንዘብ ከኪሳቸው እያወጡ ነው ሲልኩና ሲከፍሉ የነበሩት? እነርሱማ ውጭ ካለው ስደተኛ ላይ የሚሰበሰበውን ገንዘብ 5 ሺህ ለአቶ ብርሃነ መዋ 5 ሺህ ለአንዳርጋቸው ጽጌ በየወሩ ይከፈላቸው እንደነበር ከረንት አፌርስ ላይ ሲነገር የሰነበት ነገር ነው።

እነሱስ ለመሆኑ የብርሃኑ ነጋ መጽሀፍ ለቅንጅት ትግል መርጃ ተብሎ ሲቸበቸቡ የነበረው የት ገባ በምን ላይ ዋለ? እስቲ ግልጽነት ካለ ምን ያህል መጽሀፍ ተሸጠ? ምን ያህል ወጣ ምን ያህል ገቢ ሆነ? በምን ላይ ዋለ ለምን አያስታውቁም? ዛሬ የሚሰበስቡትስ ምን ሊያደርጉበት ነው ሌላ ድርጅት ሊያቋቁሙበት? ለካድሬዎቻቸው ሊሰጡት? እኮ ለምንድነው? ሌላው ተጠያቂ እነርሱ የማይጠየቁ ያደረጋቸው ማነው? እዚህ ላይ ሁለት ነገር አለ ትልቁ ሥራቸው ቅንጅትን የሚረዳውን ኃይል መበታተንና ማፈረስ ስለሆነ የገንዘብ ነገር ሲነሳ ደግሞ ሁሉም ገንዘቤ ከተበላ ለምን እሰጣለሁ ብሎ እንደሚያፈገፍግ ስለሚያውቁ የገንዘብ ተዘረፈ ዘመቻ ያካሄዱት በጥናት የተደረገ የማፍረሻ ሥልት መሆኑን በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል።

ለመሆኑ ለፓርቲውና ለሕዝብ መርጃ የተዋጣው ገንዘብ ሲባክን ያሰባሰቡትና ያዋጡት በየከተማው ያሉት የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ገንዘብ ይዘረፍ ብለው ዝም የሚሉ ይመስላችኋል? አይሉም። ገንዘቡን ደክመው ለፍተው ዓላማ ላለው ነገር ለማዋል እኮ ነው ያዋጡት። ገንዘብ ባከነ ወደ ተዘረፈ አደገ። መጀመሪያ 250 ሺ ቀጥሎ 800 ሺህ አሁን ደግሞ 1.2 ሚሊዮን ይላሉ። ኢዲተር ተብዬው ገንዘብ ጎደለ ሲል ሂሳቡን መርምሮ ነው? አስፈላጊው ዶክመንት ታይቶ ነው? ዶክመንት አልሰጥም አሉ ካለ ደግሞ የጎደለውንም አያውቅ ማለት ነው። ታዲያ የየት አገር ኢዲተር ነው በዲሲ ሬዲዮ፣ በፓልቶክና በኢትዮጵያ ሪቪው ድኅረ ገጽ ያልመረመረውን ሂሳብ ሪፖርት የሚያቀርበው? አዬ አያ ኦዲተር ከኦገስቱ 18 ቀን 2006 ስብሰባ በፊት በቴሌኮንፈረንስ ከነብርሃነ መዋ ጋር ስትዶልት ያልተሰማህ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ድራማ ነበር። ስትዶልቱ የነበረው በማስረጃ ያልተያዘ ይመስልሃል? በየትኛው የአካውንቲግ ህግና አሰራር ነው በቃል የኦዲት ሪፖርት የሚቀርበው? ለመሆኑ ኦዲተሩን መጀመሪያ ማን ቀጠረው? መልሱ ሻለቃ ዮሴፍ ናቸው። ለማነውስ ሪፖርት የሚያቀርበው? መልሱን ኦዲተሩ ይናገር። ከስራው ከተሰናበተ ከአንድ ወር 18 ቀን በኋላ በዲሲ ከነብርሃነ መዋ ጋንግስተሮች ጋር ያደረገው የቴሌኮንፈረንስ ዱለታ ወንጀልና ራሱን የሚያስጠይቀው ነው። አዎን ሻለቃ ዮሴፍን ገንዘብ ዘረፉ በማለት የጮኹት እኮ እነ ብርሃነ መዋ፣ ሞገስ ገብረማርያም፣ አንዳርጋቸው ጽጌ እና የከረንት አፌርስ የስድብና የስም አጥፊ ኤክስፐርቶች ናቸው። የዛሬው የኩዴታ መሀንዲሶች ደግሞ በአለቃቸው ታዘው ነው። አለቃቸው ደግሞ አንዳርጋቸው ጽጌ ደጋግመው እንደተናገሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ መሆናቸው ነው። በርቱ መልካም ሥራ ሁላችሁም በመፈንቅለ ፓርቲ አመራር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ትይዛላችሁ የተባሉ ይመስላሉ።

ቃሊቲ ከታሰሩት መሪዎች ማካከልና ውጭ ባሉ የወያኔ ጉዳይ ፈጻሚዎች አማካኝነት ዱለታው ሴራው በለንደን በዋሽንግተን ዲሲና በቃሊቲ ከዳተኞች መካከል ነበር። ግንቦት 14 ቀን ከቃሊቲ መጣ የተባለው የኢሜይል ሹመት ኤልያስ ክፍሌ ከማውጣቱ አንድ ወር ቀደም ብሎ እነ አንዳርጋቸው ጽጌ በኤፕሪል 13 እና 14 ላይ ጀርመን ውስጥ ዎርክ ሾፕ አድረገው ያወጡትን ዶክመንት ወደ ዋሽንግተን ዲሲና አዲስ አበባ መላኩን እናውቃለን። ቃሊቲ ተልኮ መሪዎቻችን ስለፈቀዱ ተባለና በሜይ ላይ ይፋ ሲሆን የሹመቱ ደብዳቤ የአራት ሰዎች ስም አለበት የሊቀመንበሩ፣ የምክትሏና

የጸሀፊው አራተኛው ስም ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ይላል። ዶክተር ብርሃኑ የሚለው ስም ምን ሊያደርግ ደብጳቤው ላይ ወጣ? ልብ በሉ የሥራ አስፈጻሚው አካል አይደሉም ምን አግብቷቸው የሳቸው ስም ተጠቀሰ ? ሌሎችም የሥራ አስኪያጅ አመራር እያሉ የወጣው ከንቲባ ሆነው የተመረጡት የዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው። ይህ በጭራሽ ሊሆን የማይችልና አግባብነት የሌለው ነው። ጠርጥር ይልሃል እንግዲህ ከዚህ ይጀምራል። የውጭውን ትርምስ ከዚህ በፊት በሰፊው ጽፌዋለሁ ብዙ ሰዎችም የተለያዩ ጽሁፎችን አቅርበዋል። ቃሊቲ ጀግና ብቻ ሳይሆን ከዳተኛው፣ ሥልጣን ፈላጊውና የውጭ ጠላት መሳሪያውም አብሮ ታስረል።

ኖቬምበር መጀመሪያ ላይ የታሰሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በአምስት ወር ውስጥ ባለ ስድስት መቶ ገጽ መጽሐፍ ጽፈው፣ ደብቀው አውጥተው፣ ታትሞ የተቆረጠ የኢትዮጵያ ካርታን ይዞ በተዓምር ዓለምን አዳረሰ። አጀብ ! እስቲ ወገኖቼ የታሰረ እስረኛ ለዚያውም 3 ሳምንት ነው ወር ገደማ ሆስፒታል የነበረ እስረኛ መጽሐፍ ጽፎ ለንባብ አበቃ ? ዶክተር ብርሃኑ መጽሐፉን ለመጻፍ እውቀት ወይም ችሎታ የላቸውም አይደለም አባባሌ እንዴት እና የቃሊቲው እስር ቤት የደህነት አጠባበቅ ወይም የሴኩሪቲው ሁኔታስ ለእሳቸው ምን ያህል አመቺ ሆኖ ነው ጽፈው አርመው ለአንዳርጋቸው ጽጌ ተልከ ታርሞ ማተሚያ ቤት ተዋውለው ታትሞ አገር ቤት በድብቅ ገብቶ ለሕዝብ በድብቅ ተሰራጭቶ ውጭ ያለነው ካገር ቤት ላኩልን ብለን ተራኩተን ያገኘነው። መቼም እንዴት ያለ ድራማ ሰሩብን እባካችሁ። አጃጃሉን አኮ እነ አቶ በትናቸው ጽጌ ወይም አንዳርጋቸው ጽጌ። የሚገርመው ለመጠራጠርና እንዴት ተቻለ የሚለውን ሳናነሳ የእነርሱ ካድሬዎች በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የፖለቲካ እስረኛ መጽሐፍ ጻፈ ያሉትን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሆነን መጽሀፉን ለማግኘት ተራኮትን። የአብዛኞቻችን ችግር ሁሌም አፈኛ እንዳታለለን እንኖራለን። ነፍሱን ይማረውና አቶ ክህደቱ አያሌውን ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። የዛሬውም ከዳተኞች እና የጠላት መሳሪያዎች በአካል መሞታቸው ይቀላቸው ነበር በሕዝብ ተጠልተውና ተዋርደወ የቁም ሞት ከሚሞቱ።

ስለ መጽሐፉ ካነሳሁ አንዲት ነገር ልጥቀስ፤ ስድስት ወር እስር ቤት የታሰረ ሰው እንዴት ነው አንዲት ምዕራፍ እንኳን ስለ እስር ቤቱ ስቃይ፣ ጽዳት፣ የእስረኛ ብዛት፣ የምግብ ሁኔታ፣ መንገላታት፣ የፖሊሶች ሁኔታ፣ የዘመድ ጥያቂው ጉዳይ በአጠቃላይ አናኗሩ አንዳችም ሳይጠቀስ ከ30 ዓመት በፊት በኢሕአፓ ጊዜ የነበረን ታሪክ በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ ተጠቅሶ ከዚያም በምርጫው ዘመቻ ላይ እኔ እኔ እኔ የሚለው ሰድስት መቶ ጊዜ ሲጠቀስ ሌላው የለፉበት መስዋዕት የከፈለበት ሳይነገር የአቶ ኃይሉ ሻውልና የልደቱ አለመግባባት እና ችግር መፍጠር ተደጋግሞ ሲጠቀስ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ መፍትሔ ፈላጊና አስታራቂነት ከቅንጅቱ ታሪክ በላይ ሲደረደር ወቼው ጉድ ከማለት ሌላ ምን ይባላል። አንዳርጋቸው ጽጌ ያሉት ለንደን ብርሃኑ ነጋ ያሉት ቃሊቲ የመጽሐፉ ሁኔታ አልጋ ባልጋ ሆነና ግሩም ድንቅ ተባለ ዓለምን አታለለ። እውነቱ ግን ከዚያ የተለየ ነው። መጽሐፉም እንደተባለው ታንዛኒያም አልታተመ። አስመራ ነው የሚል መረጃ በቅርቡ ተገኝቷል። እነ አንዳርጋቸው ጽጌ እና ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የተቀነባበረ ሴራቸውን ሲዶልቱ፣ ቅንጅትን ሲከፋፍሉ፣ ሲያዳክሙ የቆዩት በውጭ ኃይልና እና በወያኔ ኃይል ነበር። ብዙ ጉድ እያደር ይሰማል። የዶክተር ብርሃኑ መጽሐፍ ከመውጣቱ በፊት ሌላ አስተዋዋቂ መጽሐፍ የግንቦት ሰባቱ ምርጫ የሚል በክፍሉ ታደሰ መውጣቱ የተቀነባበረ እና ብርሃነ መዋን አንዳርጋቸው ጽጌንና ብርሃኑ ነጋን ፕሮፋይል ከፍ ለማድረግ የታቀደ ቅድመ ብርሃኑ ነጋ መፅሐፍ ማስተዋወቂያ መሆኑን ብዙዎች ይናገሩታል።

ወያኔ ሲገባ 41 የየዩንቨርስቲ መምህራን ሲያባርር እንደ እነ እንድርያስ እሸቴ አይነቶችን ከሃዲ ባንዳዎች ሲቀጥርና ሲሾም ሌሎች 19 ሰዎች ደግሞ ከውጭው ዓለም መጥተው ቦታቸውን ይዘዋል። ከእነዚህ አንዱ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ናቸው። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከወያኔ ጋር እጅና ጓንት ሆነው ሲሰሩና በንግዱም ዓለም ሚሊየነር ለመሆን ሲበቁ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆመው አንድም ቀን አገር ተገነጠለ፣ ሕዝብ በዘር ተከፋፋለ በጎሳ ተጨራረሰ ሳይሉ ሕዝብ ሲያልቅ ድምጽ ያላሰሙ፣አገር ስትጠፋ ቃል ያልተነፈሱ ከእነ በረከት ስምዖንና ከመሰል ዜናዊ ጋር ቴኒስ ሲጫወቱ ጋደኛ ሆነው የከረሙ ናቸው። አዎን በ1994 ለዩንቨርስተ ተማሪዎች ንግግር አደረጉ ተብለው

ከፕሮፌሰር መሥፍን ጋር ለ 28 ቀን መታሰራቸው ይታወሳል:: ከዚያ በኋላ ብቅ ያሉት የ 1997 ምርጫ ሊካሄድ 8 ወር ሲቀረው ነው:: ድሮም ብርሃኑ ነጋ ቅንጅት ያሸንፋል ብለው አላመኑም:: የአዲስ አበባን ከተማ ውድድር አሸንፈው ከነበረከት ጋር እየተጋፉ ከንቲባ ሆነው መኖር ነበር ሀሳባቸው:: በምርጫውም ዘመቻ ጊዜም ሆነ ከምርጫው በኋላ ከውጭ ጌቶቻቸው የሚሰጣቸውን መመሪያ ከአሜሪካን አምባሳደርዋ ቪኪ ስር ስር ሲሉና ሲቀበሉ የቆዩ መሆናቸው ይታወሳል:: አንዳንዴ አስቸጋሪነቱ አንዱን እናጋልጣለን ሲባል የደህና አገር ወዳድ ዜጎች ደህንነት አብሮ ለአደጋ ይጋለጣል በሚል እየታወቀ ለብዙ ጊዜ ሲያዝ እነርሱ ብዙ ዜጋ ለማወናበድ ጊዜ ሰጣቸው:: እስቲ ዶክተር ብርሃኑን ነጋን ለረጂም ጊዜ የሚያውቁ ኢትዮጵያዊ ስለእሳቸው ለሌላ ሰው በእንግሊዝኛ የጻፉትን ቀንጭቤ ላቅርብ:: እንዲህ ይላል "Believe it or not there is no division in KIC as you describe it. Furthermore, indeed, Ato Hilue Shawel is the legitimate elected leader of Ethiopia. For sure Berhanu is not our freedom fighter. He does not have the hearts and minds of Millions of Ethiopians. Let's not single out Berhanu Nega's case and dual on his patriotism?

Berhanu is not an honest advocate of Democracy. He is a sectarian and opportunist. Brehanu had worked very closely with Meles and the Woyanes. He was a perfect fit to Meles. He served them well like hands and gloves. He is responsible for what has happening in Ethiopia for the last 20 years. He is also responsible to the current CUDP crisis. He is opportunist and power monger. We all know his position and he is "Ye Keberro Bahitawie or the Wolf in Sheep clothing." Personally I know Berhanu Nega when he was the Military government agent in Debre Zeite and Addis Ababa in the late 1970's. He was part of the National Communist League, whose soul purpose was to infiltrate the youth and spy on their activities against EPRP members. Because of him many innocent students were killed both in Debre Zeit and Addis Ababa. Later I met him in the Sudan as a refugee. While he was in the Sudan he reached out to the opposition parties against the Military government and he became a double agent. Later I met him in the USA and shared numerous political forums such as the "Horn of Africa in New York, Berrana Pennsylvania, and many political activities Washington D.C. areas. While he was a student at the New School for Social Research, in New York City, he not only organized anti Ethiopian forums but also in coalition with his professors, he sponsored and financed the TPLF and EPRDF activities in New York and North East United States. He further publicized their activities and anti Ethiopian sentiments through conservatives and anti socialist organization publications. In fact he and his friends worked so hard for the success of Melees at the expresses of the rest of TPLF leadership as shown in Canada, London and Washington D.C. etc.

When, the Woyanes, took over we both returned to Ethiopia to serve our country. He returned Ethiopia with lots of money and hired by the CIA and as the supporter of the Woyanes.. While I continued my life as a private citizen, Berhanu Nega became an Overnight Star with Dr. Mulue Kestella. Both became not only advisers to Melees but best friends who shared the same values and visions for Ethiopia. For 14 years, they worked with Woyane and became part and parcels of the destructive force. My advice to Dr. Berhanu Nega is to stay out of Ethiopian politics. He is on a mission for the CIA. He is also a Multi Millionaire. He does not stand for CUD's principles and objectives. He is a Woyane employee!"

እስር ቤት እያሉም በውጭ ያሉ የቅንጅት ደጋፊዎች እንዲከፋፈሉ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ እና ትእዛዝ ሲሰጡ የነበሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነበሩ:: አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እኔ የምቀበለው የመሪዬን የብርሃኑን ነጋን ትእዛዝ ነው ብለው በተደጋጋሚ ሲናገሩ ነበር ዛሬም ይናገሩታል:: የቅንጅት መሪ ብርሃኑ ነጋ አይደሉም ኃይሉ ሻውል እንጂ::

ሌላው እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የታሰሩት እነ ኢንጂነር ኃይሉ ከታሰሩበት ክፍል በተለየ ነበር:: የአጋጣሚ ይሆን? ይመስላል ግን አይደለም:: ብርሃኑ ነጋ ከእስር ቤት እየወጡ

እቤታቸው የሚያድሩበት ጊዜ እነደነበር፤ "ትፈለጋለህ" እየተባሉ ማታ ማታ ይወጡ እንደነበር ቃሊቲ የነበሩት ይናገራሉ፡፡ ከእነ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋርም በቴሌኮንፈረንስ ይገናኙ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ኅበዝ መጠርጠር አይከፋም ምንድነው የተደገሰልን ምንድነው የተዶለተብን? ይህን መጠየቅና ማወቅ ይገባናን፡፡ የቀድሞ ወያኔ ደጋፊዎች በድብቅ ተሰባስበው የረቀቀ ሴራ አዘጋጅተው የሀሰት ጀግና ፈጥረው ስሙን ሰማይ አድርሰው ሕዝቡ ያንን የሀሰት ጀግና ሲከተል እንዲቆይና ከወያኔ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ሲረዳ በብስጭትና በሀዘን ተስፋ ቆርጦ ትግሉን ከድቶ እንዲቀመጥ የታቀደ ደባ ነው፡፡ ከእስር ቤት ወጣ የተባለው ጽሑፍ ሁሉ ጻፉ የተባሉት ግለሰቦች ያልጻፏትና ፕሮፋይላቸውን ከፍ ለማድረግ የታቀደ ሀሰት ነው፡፡ ጠንቀቅ እንበል እናስተውል፡፡ ከውስጥ እነብርሃኑ ነጋ ጥቂት አብረው በጥቅምና በፍርሃት ከተያዙ ሰዎች ጋር ሆነው ውጭ ባሉ ደጋፊዎቻቸው ተባባሪነት መፈንቅለ ፓርቲ እያደረጉ ነውና፤ ከወያኔ ጋር እንደራደር፣ ተስማምተን ለሚቀጥለው ምርጫ እንዘጋጅ፣ የቅንጅት አመራር ኃላፊነቱ ለወጣቱ ክፍል ይሰጥ የሚሉንን ነቅተን መጠበቅ፣ ማጋለጥና ማሳፈር ይኖርብናል፡፡ የወያኔ ገንዘብ በሥራ ላይ መዋሉን እያየን ነውና ማንቀላፋቱና ዝም ማለቱ ይብቃ፡፡ ሀቀኛ የሕዝብ ልጆችንና መሪዎችን አሳልፈን ሳንሰጥ ደግፈናቸው ትግሉን ከግቡ ለማድረስ በቆራጥነት እንነሳ፡፡

የጽሑፉ ዓላማ መጋለጥ ያለባቸው እንዲጋለጡ፣ ማስተዋል ያነሳቸው እንዲያስተውሉ፣ መማር ያለባቸው እንዲማሩና የተወናበዱ እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡ ባለማወቅ አብራችሁ የተሰለፋችሁ ሰዎች ራሳችሁን መርምሩ ወይ የሕዝብን አደራ ተወጡ አሊያም አደራውን አስረክቡ እንላለን፡፡ የሕዝብ ተመራጮች የሆናችሁ ሁሉ መታሰር ብቻውን ጀግና እና መሪ አያሰኝም ለሕዝብ አደራ መቆም እንጂ፡፡ የሚያኮራው የሚያስከብረው የሚያስወድደው ከመረጣችሁ ሕዝብ ጋራ መቆም እንጂ፡፡ ያንን የሕዝብ አደራ ሳታከብሩ በአገር ቤትም በውጭም መከበር የለም፡፡

አንድ ነገር በእርግጠኛነት ልናገር፡፡ ቅንጅት አይከፋፈልም፡፡ ተከፍሎ ቁራጩን ይዘው ለመጓዝ የሚፈልጉ ሁሉ እርማቸውን ያውጡ፡፡ ሴረኞቹ ይወገዳሉ፡፡ የኢትዮጵያና የአንድነት ኃይሎች በአሸናፊነት ይወጣሉ፡፡ የወያኔን እድሜ በተዘዋዋሪ ለማራዘምና የሀሰት ጀግና ሆነው በሕዝብ ስም ሊነግዱ የሚፈልጉ ሁሉ ያፍራሉ፡፡ ከሚቹ ልደቱ አያሌው አልተማሩምና በቅርቡ ይቀላቀሉታል፡፡ መልካም ቅልቅል፡፡

ከሀቀኛ የቅንጅት መሪዎች ጋር ወደፊት!
ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት ትኖራለች !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !